

# Triple P:

## Positive Parenting Program (አወንታዊ የማደጎ ፕሮግራም)

### ስለ አገልግሎቱ

Triple P ወላጆችን መሰረት ያደረገ መፍትሄ ተኮር አገልግሎት ሲሆን፣ አሳዳጊዎች ፈታኝ የሆኑ የወላጅነት ሁኔታዎችን በአስተማማኝ ሁኔታ ለመቆጣጠር የተለያዩ መንገዶችን እንዲማሩ ያደርጋል። ፕሮግራሙ በአብዛኛው ከ10 እስከ 14 ሳምንታዊ ክፍለ ጊዜዎችን ያካተተ ሲሆን፣ እያንዳንዱ ክፍለ ጊዜ ከ50 እስከ 90 ደቂቃዎች ይቆያል። ቤተሰቦች ግባቸውን እንዲያሳኩ ለመርዳት፤ የጋብቻ አጋር ድጋፍ፣ የመቋቋም ክህሎቶች ወይም ተጨማሪ የመለማመጃ ክፍለ-ጊዜዎች ሊኖሩ ይችላሉ።

### አገልግሎቱ የሚጠቅመው ማንን ነው?

ወላጆችን፣ ዘመድ ቤተሰቦችን፣ የጉዲፈቻ ቤተሰቦችን እና ከ2 እስከ 18 ዓመት እድሜ ያላቸው ልጆች ያሏቸው፣ በልጃቸው ባህሪ መካከለኛ እና ጉልህ የሆኑ ተግዳሮቶችን የሚያጋጥማቸው እና ከልጃቸው ጋር ያላቸውን ግንኙነት ማሻሻል የሚፈልጉ የማደጎ ቤተሰቦችን።

### የአገልግሎቱ ዋና ዋና ነጥቦች

- ፕሮግራሙ የልጅ እድገትን እና የወላጅና-ልጅ ግንኙነትን ይደግፋል
- በልጅ እንክብካቤ ላይ ያላቸውን ልበ-ሙሉነት እንዲጨምር ይረዳል።
- የወላጆችን እና ልጆችን ትልልቅ ተግዳሮቶች እንዲሁም ጥንካሬዎች ይገመግማል
- ችግሮቹን እያስከተለ ያለው ምን እንደሆነ እና ውጤቱ/ግቦቹ ምን እንደሆኑ ወላጆች እንዲለዩ ይደግፋል
- አወንታዊ ባህሪያትን የሚያበረታቱ ስልቶችን እና የባህሪ ችግሮችን እንዴት መቆጣጠር እንደሚቻል ያስተምራል
- የተለያዩ አወንታዊ የወላጅነት ክህሎቶችን ያስተዋውቃል
- ውጤታማ የወላጅነት ልማዶችን ለማዳበር ክህሎቶችን እና ስልቶችን የመለማመድ እድል ይሰጣል
- ብዙ ቤተሰቦች ፈታኝ ሆኖ የሚያገኙትን “ከፍተኛ ስጋት” ያላቸውን ሁኔታዎች ለመቆጣጠር ስልቶችን ይፈጥራል
- የትምህርት ክፍለ-ጊዜዎች የተለመዱ የወላጅነት ወጥመዶችን ለማስወገድ የሚረዱ ክህሎቶችን፣ የብስጭት/የጭንቀት ስሜቶችን ለመቆጣጠር ስልቶችን እና በወላጅነት ውስጥ የቁጣ/ጭንቀት ሚናን መረዳትን ሊያካትቱ ይችላሉ
- ተሳታፊዎች ለለውጥ ግቦችን ያወጣሉ

### ድጋፍ

ልጆች እና ቤተሰቦች የልጆችን ደህንነት የሚደግፉ፣ የጥቃት ወይም የቸልተኝነት አደጋን የሚቀንሱ፣ የቤተሰብ መረጋጋትን የሚያረጋግጡ ወይም ደህንነቱ የተጠበቀ መገናኘትን የሚያመቻቹ ቁሳቁሶችን እንዲያገኙ ለመርዳት፣ እስከ $500 ሊገኝ ይችላል።

*DCYF ለሁሉም ለፕሮግራሞቹ እና አገልግሎቶቹ ዘር፣ ቀለም፣ ጾታ፣ ሃይማኖት፣ እምነት፣ የጋብቻ ሁኔታ፣ የዜግነት ሁኔታ፣ የዜግነት ወይም የኢሚግሬሽን ሁኔታ፣ ዕድሜ፣ የጾታዊ ዝንባሌ ወይም የጾታ ማንነት፣ እድሜ፣ የውትድርና እና የመከካከያ ሁኔታ፣ እንደ ጡት የምታጠባ እናት ሁኔታ ወይም የምንም አይነት አካላዊ፣ ስሜታዊ፣ ወይም የአዕምሮ እክልን በማየት እና የውሻ መመሪያ ወይም የአገልግሎት እንስሳ በመጠቀም አያዳላም እንዲሁም እኩል ተደራሽነትን ያቀርባል። የዚህን እትም ነፃ ቅጂዎች በሌላ ቅርጽ ወይም ቋንቋ ማግኘት ከፈለጉ፣ እባክዎ DCYF የደንበኞች ግንኙነትን በ 1-800-723-4831 ያግኙ ወይም ኢሜይል **communications@dcyf.wa.gov** ያድርጉ*

Washington State Department of
CHILDREN, YOUTH & FAMILIES

DCYF PUBLICATION PPS_0067 AM (07-2024) Amharic